# በኢፌዴሪ የትምህርት ሚኒስቴር
# የቅድመ መደበኛ ትምህርት (አፀደ ህጻናት)
# ስታንዳርድ

ግንቦት 2010

ትምህርት ሚኒስቴር

**ማውጫ** **ገፅ**

## ክፍል አንድ

1.1 መግቢያ........................................................................................ 1

1.2 አጠቃላይ ዓላማ................................................................................ 2

1.2.1 ዝርዝር ዓላማዎች.............................................................................. 2

1.3 አስፈላጊነት...................................................................................... 2

1.4 የተፈፃሚነት ወሰን.............................................................................. 3


## ክፍል ሁለት

**2.የቅድመ መደበኛ ትምህርት ተቋማት የሚቋቋሙባቸው አካባቢዎችና**

**የሕንፃው ሁኔታ.................................................................................. 4**

2.1.የቦታ አመራረጥ.................................................................. 4

2.2 የምድረ ግቢ ገጽታና አደረጃጀት............................................................ 4

2.3 የቅድመ መደበኛ ትምህርት ተቋማት መጠን........................................ 5

2.4 የመማሪያ ክፍል/ክፍሎች ........................................................................ 5

2.5 የአገልግሎት መስጫ ክፍሎች................................................................. 6

2.6 ለልዩ ልዩ ክፍሎች አስፈላጊ መሣሪያዎች.............................................. 8


## ክፍል ሶስት

**3. የሰው ኃይል ምደባ................................................................................ .. 15**

3.1 የመምህራንና ሠራተኞች ምደባ.......................................................... 15

3.2 የመምህራንና የሠራተኞች የትምህርት ደረጃ........................................ 16


## ክፍል አራት

**4.1 የቅድመ መደበኛ ትምህርት መርሀ ግብር ፕሮግራም.............................. .... 17**

**4.2 የፕሮግራሙ አወቃቀር/አደረጃጀት.............................................................. 17**

**4.3 የቅድመ መደበኛ ትምህርት መርሀ ግብር የትኩረት አቅጣጫዎች... ........ 18**

**4.4 የቅድመ መደበኛ ትምህርት አቀራረብ........................................................ 18**

4.4.1 ነፃና የታቀደ ጨዋታ...................................................................... 18

4.4.2 በክፍልና ከክፍል ውጭ ተቀናጅተው የሚሰጡ የትምህርት አይነቶች.... 19

4.4.3 ግላዊና ማህበራዊ ጠቀሜታ ያለው ሥራዎች...................................... 19

**4.5 ለልዩ ፍላጎት ሕፃናት....................................................................... ... 19**

4.5.1 ለአይነ ስውራን................................................................................. 19

4.5.2 መስማት ለተሳናቸው.......................................................................... 20

4.5.3 የአእምሮ ዕድገት ውስንነት ላለባቸው............................................ 20
4.5.4 አካላዊ ጉዳት ችግር ላለባቸው...................................................... 21
4.5.5 ከሌሎች ጋር የመግባባት / የመናገር/ ችግር ላለባቸው.................... 21
4.5.6 የባህርይ እና ማህበራዊ ችግር ላለባቸው........................................ 21
4.5.7 የመማርና የማንበብ ችግር ላለባቸው.............................................. 21
4.5.8 የመማር ችግር ያለባቸው................................................................ 21
4.5.9 የመናገር ችግር ያለባቸው.............................................................. 21
4.5.10 የአካል ላይ ጉዳት (Physical or Orthopedic Impairment) ያለባቸው.......................................................................................... 22
4.5.11 የሚጥል ችግር ያለባቸው............................................................ 22
4.5.12 ኦቲስቲክ የሆኑ ልጆች............................................................... 22
4.5.13 ተደራራቢ የአካል ጉዳት ላለባቸው.............................................. 22
4.5.14 የስሜት መረበሽ ያለባቸው......................................................... 23
4.5.15 ልዩ ተሰጥኦ ያላቸው.................................................................... 23
**4.6. አመታዊ የትምህርት መርሀ ግብር /ካሌንደር/............................................ 23**
4.6.1 የቅድመ መደበኛ ትምህርት ፕሮግራም ደረጃዎች.......................................... 23
4.6.2 የክፍለ ጊዜያት ሥርጭት.............................................................................. 24
4.6.3 የመምህራን የሥራ ሰዓት.............................................................................. 26
**4.7 የትምህርት ቋንቋ የማስተማርና የምዘና ዘዴዎች.......................................... 27**
4.7.1 የትምህርት ቋንቋ.......................................................................................... 27
4.7.2 የማስተማር ዘዴዎች...................................................................................... 27
4.7.3 የምዘና ዘዴዎች............................................................................................ 28
4.7.4 ክፍል መድገምን በተመለከተ.......................................................................... 28
4.7.5 ከክፍል ክፍል ዝውውር.................................................................................. 28
4.7.6 የተማሪ ቅበላን በተመለከተ............................................................................ 28
4.7.7 የማበረታቻ እና የምስክር ወረቀት.................................................................. 29
4.7.8 ግላዊ መረጃ አያያዝን በተመለከተ.................................................................. 29

## ክፍል አምስት

5. ከቅድመ መደበኛ ትምህርት መምህራን የሚጠበቅ ባህርይ እና የትምህርት ዝግጅት.......................................................................... 30
5.1 ከቅድመ መደበኛ ትምህርት መምህራን የሚጠበቅ ባህርይ.......................... 30
5.2 የቅድመ መደበኛ መርሐ-ግብርን ያጠናቀቁ ሕፃናት ባህርይ....................... 30

DRAFT

ሰንጠረዥ

ሰንጠረዥ 1:- በአፀደ ህጻናትሊኖሩ የሚገባቸው የአገልግሎት መስጫ ክፍሎች

ሰንጠረዥ 2:- ለአንድ መማሪያ ክፍል የሚያስፈልጉ ቋሚ መሣሪያዎች፣

ሰንጠረዥ 3:- ከህፃናት ተማሪዎች ጋር የተያያዙ መረጃዎች

ሰንጠረዥ 4:- የመማሪያ መፃህፍት በአይነትና በምጣኔ፣

ሰንጠረዥ 5:- የመጀመሪያ ደረጃ ሕክምና ዕርዳታ መስጫ ዕቃዎች በአይነትና በብዛት

ሰንጠረዥ 6:- ለመጀመሪያ ሕክምና ዕርዳታ መስጫ ክፍል የሚያስፈልጉ መድኃኒቶች

ሰንጠረዥ 7:- ለማዕድ ቤት የሚያስፈልጉ ዕቃዎች በአይነትና በብዛት

ሰንጠረዥ8 :- የትምህርት እና የጨዋታ ማዕዘኖች በአይነትና በብዛት

ሰንጠረዥ 9 :- ቋሚ የውጭ መጫወቻ መሣሪያዎች በአይነትና በብዛት

ሰንጠረዥ 10:- ለርዕሰ መምህርት/ር ቢሮ የሚያስፈልጉ ዕቃዎች

ሰንጠረዥ 11:- የመምህራንና ሠራተኞች ብዛት፣

ሰንጠረዥ 12:- ቅድመ መደበኛ ትምህርት መምህራንና ሰራተኞች የትምህርት ደረጃና ብዛት

ሰንጠረዥ 13 :- ሣምንታዊ የክፍል ጊዜ ሥርጭት በደረጃ

ሰንጠረዥ 14 :- ዕለታዊ መርሃ ግብር በደረጃ

DRAFT

# ክፍል አንድ

## 1.1 መግቢያ

ዘመናዊ የትምህርት አጀማመር በኢትዮጵያ በወቅቱ ከነበሩ አዳዲስ አስተሳሰቦችና ፍላጎቶች እንዲሁም በዓለም ላይ የነበረው የኢኮኖሚያዊ፣ ባህላዊና ፖለቲካዊ ሁኔታዎች ነፀብራቅ እንደሆነ ከታሪክ መጻህፍትና ከተደረጉ ጥናትና ምርምሮች መረዳት ይቻላል። በአጭር አገላለፅ የአመታትን ብዛት እንደ ማስረጃ በመወሰድ ዘመናዊ ትምህርት በኢትዮጵያ ከተጀመረ ከ100 ዓመት /ከአንድ ክፍለ ዘመን/ የዘለለ እድሜ ያለው መሆኑን መገንዘብ ይቻላል።

የቅድመ መደበኛ ትምህርት አጀማመርም ተመሳሳይ ባህርይ ቢኖረውም የተለያዩ ደመቀ ጥናታዊ ፅሁፎች የመጀመሪያው የቅድመ መደበኛ ትምህርት እንደ ኤሮፓ አቆጣጠር ከ1900 በፊት በድሬዳዋ እንደተጀመረ ያሳያሉ ።

የቅድመ መደበኛ ትምህርት የህጻናትን አካላዊ ፣ ስነልቦናዊ፣ ማህበራዊ፣ አእምሯዊ እና ስሜታዊ እድገቶች የተስተካለለ በማድረግና በመደበኛነት ለሚሰጠው ትምህርት ዝግጁ በማድረግ ለወደፊቱ የትምህርት እና የህይወት ዘመናቸው መሰረት የሚጣልበት አንዱና መሰረታዊ የህይወት የእርከን ደረጃ ነው።

በየደረጃው እንደ ሀገር የተቀመጡ የትምህርት ግቦችን ለማሳካት አንድ የትምህርት ፕሮግራም ደረጃውን የጠበቀ ነው ለማለት የሚቻለው በተቀመጠለት መለኪያ /ስታንዳርድ/ መሰረት ተግባራዊ መሆኑ ሲረጋገጥ ነው። ከዚህ በተጨማሪ የአንድ አገር የትምህርት ጥራት ደረጃ ሊመዘን የሚችለው እንደ ሀገር ስራ ላይ እንዲውል ከወጣው የደረጃ መለኪያ /ስታንዳርድ/ አኳያ ሲገመገም፣ ተመሳሳይ ስታንዳርድ ካላቸው አገሮች አኳያ ተነፃፅሮ ሲታይና የተሻለ ስታንዳርድ እየተጠቀሙ ነው ከሚባሉት አገሮች ጋር ሲገናዘብ ነው።

የመንግስትም ሆኑ የግል የቅድመ መደበኛ ትምህርት ተቋማት ትምህርትን በጥራትና በፍትሀዊነት መስጠት እንዲችሉ ከተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ማለትም ከስርአተ ትምህርት፣ ከሰው ሀይል፣ ከትምህርት መሳሪያዎች አቅርቦት፣ከመማሪያ እና አገልግሎት መስጫ ከፍሎች እና ከመሳሰሉት ጋር የተያያዙ ግብአቶችን በማሟላት እና ጠንካራ የትምህርት አመራርና አስተዳደር ስርአት በመዘርጋት ስራ ላይ ማዋል ይጠበቅባቸዋል።

በመሆኑም አንድ የቅድመ መደበኛ ትምህርት ተቋም በዝቅተኛ ደረጃ ማሟላት ያለበትን ስታንዳርድ በማሟላት ህፃናት በደረጃቸው በእውቀት፣ በአስተሳሰብ እና በክሂሎት በልፅገው

ለመደበኛው ትምህርትቤት ዝግጁ እንዲሆኑ ለማድረግ እንዲቻል ይህ ስታንዳርድ ተሻሽሎ ተዘጋጅቷል።

## 1.2 አጠቃላይ ዓላማ

የቅድመ መደበኛ ትምህርት  የሚሰጡ ተቋማት በሀገር አቀፍ ደረጃ ወጥነት ያለውና ደረጃውን የጠበቀ  አገልግሎት በመስጠት ህፃናት ለደረጃው ተገቢነትና ጥራት ያለው የትምህርትና ጨዋታ አገልግሎት በመስጠት በዝቅተኛ ደረጃ ለህጻናት ሁለንተናዊ እድገት የሚያስፈልጉ ግብአቶችና አገልግሎቶች ማሟላታቸውን ማረጋገጥ ነው።

### 1.2.1 ዝርዝር ዓላማዎች

በቅድመ መደበኛ ትምህርት አገልግሎት ላይ የተሰማሩ ተቋማት/ አፀደ ህፃናት

- የቅድመ መደበኛ ትምህርት የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲውን እና ሀገር አቀፉን ስርአተ ትምህርት መሰረት አድርጎ እየተሰጠ መሆኑን ለማረጋገጥ፣
- ር/መምህራን፣ መምህራን፣ ረዳት መምህራን፣ሞግዚቶች እና የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ለደረጃው የተቀመጠውን የትምህርት ዝግጅት ያሟሉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ፣
- ለሁሉም ህፃናት የልዩ ፍላጎት እና አካል ጉዳተኛ ህፃናትን ጨምሮ ተቋማቱ ምቹ እና በዝቅተኛ ደረጃ ማሟላት ያለባቸውን የቦታ ስፋት፣ ፋሲሊቲዎችና የአገልግሎት መስጫ ክፍሎችን ማሟላታቸውን ለማረጋገጥ፣
- ለሁሉም ህፃናት የልዩ ፍላጎት ህፃናትን ጨምሮ በዝቅተኛ ደረጃ በክፍል ውስጥ እና ከክፍል ውጪ ለመማሪያ እና ለመጫወቻ የሚያገለግሉ ቁሳቁሶች ተቋማቱ አሟልተው አገልግሎት እየሰጡ መሆኑን ለማረጋገጥ፣

## 1.3 አስፈላጊነት

ሕፃናት ከዕድሜያቸው ለጋነት የተነሳ በማንኛውም ጊዜ ከየትኛውም የሕብረተሰብ ክፍል የበለጠ ለአደጋና ለጉዳት የተጋለጡ በመሆናቸው ልዩ ጥበቃ፣እያያዝና እንክብካቤ እንደሚያስፈልጋቸው እሙን ነው። በተለይ በመጀመሪያዎቹ አምስት አመታት የሚደረግ እንክብካቤ ለህፃናት ህልውና ማለትም መኖር አለመኖር እንዲሁም ለወደፊት ዕድገታቸው ወሳኝነት እንዳለው ስለሚታመንበት ልዩ ትኩረት የሚያስፈለገው ጉዳይ ነው።ከዚህ በተጨማሪም አካል ጉዳት ያለባቸው ህፃናት ጉዳታቸው እያደጉ ሲመጡ የከፋ እንዳይሆን ቅድመ እርዳታ (Early support) እንዲያገኙና በወደፊት ትምህርትና ህይወታቸው ውጤታማ እንዲሆኑ የምናዘጋጅበት የትምህርት ዕርከን መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል።

DRAFT

ከዚህ በተጨማሪ የቅድመ - መደበኛ ትምህርት ተቋማት ሕፃናት ለወደፊት ህይወታቸው መሠረት የሚጥሉበትና ለመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ዝግጁ የሚደረጉበት ሥፍራዎች ናቸው። እንደዚሁም ሕፃናት በጋራ ተሰባስበው አንድ ላይ በሚውሉበት ወቅት የጋራ ስሜትን በማዳበር ማህበራዊ ጠቀሜታንም የሚያስገኝ ነው። በተጨማሪም እናቶች  በቂ ጊዜ እንዲኖራቸው በማድረግ በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚና በማህበራዊ ኑሮ መስክ በመሳተፍ ለአገር ግንባታ የበኩላቸውን እንዲወጡ ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ናቸው። ከዚህ አኳያ የቅድመ መደበኛ ትምህርት ፕሮግራም በወደፊቱ የአገር ኢኮኖሚ ዕድገት ላይ የሚኖረው ኢኮኖሚያዊ አስተዋጽኦ የላቀ ከመሆኑም ባሻገር በህፃናት አካላዊም ሆነ አእምሯዊ እድገት ላይ ጠንካራ መሰረት የሚጣልበት እና ማህበራዊ እኩልነትን የሚያጠናክር በመሆኑ አስፈላጊነቱ የጎላ ነው ።

## 1.4 የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ የቅድመ መደበኛ ትምህርት ስታንዳርድ በመንግስት፣ በግል፣በሀይማኖትተቋማት፣ በህዝብ፣ በግብረሰናይ፣ በህብረት ስራ ማህበራት/ ዩኒየኖች፣ እና በመሳሰሉት ድርጅቶች በተቋቋሙ አጸደ ህጻናት ተፈፃሚ ይሆናል።

DRAFT

# ክፍል ሁለት

## 2.የቅድመ መደበኛ ትምህርት ተቋማት የሚቋቋሙባቸው አካባቢዎች እና የሕንፃ ሁኔታ

### 2.1 የቦታ አመራረጥ፤

- አካባቢው የፀዳና ለሕፃናት ተስማሚ የሆነ ንጹህ አየር ያለው፣ ከቆሻሻ መጣያ፣ከፍሳሽ፣ ከወንዞች፣ ከኩሬዎች፣ ከረግረግና ከገደል የራቀና ሕፃናትን የሚተናኮሉ አውሬዎችና ነፍሳት የሌሉበት፤
- በአካል ጉዳት ምክንያት የእንቅስቃሴ ችግር ያለባቸውን ልጆች እንዲያስተናግድ ቢቻል ሜዳማ ካልተቻለ የተደለደለ፣
- ለትራፊክ አደጋ የማያጋልጥ፤
- በቀላሉ ንጹህ የመጠጥ ውሃ የሚገኝበት፤
- ከመንገድ ዳር ገባ ያለ፤
- ከመጠጥ ቤቶች እና ጫት መሸጫ 500 ሜትር የራቀ፤
- በአቅራቢያው ሆስፒታል፤ ጤና ጣቢያ ወይም ክሊኒክ ያለው ሆኖ ተላላፊ በሽታ ከሚከላከሉ እንደ ሳንባ ነቀርሳ መከላከያና ከመሳሰሉት የጤና ድርጅቶች አቅራቢያ የራቀ፣
- ፀጥታ የሰፈነበት አካባቢ፣ ከወፍጮ ቤት፣ ከሙዚቃ ቤት፣ ከገበያ፣ከፋብሪካ፣ ከብረታብረት፣ከእንጨት መሰንጠቂያ እና የጣውላ ውጤቶች ማምረቻ ድርጅቶች እና ከመሳሰሉት 500 ሜትር የራቀ፣
- ሰፊ ቦታና በቂ የመጫወቻ ሥፍራ ያለው፤
- አፀደ ህፃናቱ የሚገኝበት ቦታ በአማካይ ከህጻናቱ መኖሪያ ከ1 ኪሎ ሜትር ያልራቀ መሆን አለበት።
- የቅድመ መደበኛ ትምህርት ተቋም ሕንፃዎች እንደየአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ፣ የአየር ንብረትና የማቴሪያል አቅርቦት ከስሚንቶ፣ ከአሸዋ፣ ከብሎኬት፣ ከሸክላና ወዘተ ማቴሪያሎች ሊሠሩ ይችላሉ።

### 2.2 የምድረ ግቢ ገጽታና አደረጃጀት

- ምድረ ግቢው በአጥር የተከበረ ሆኖ ቁመቱ ከ1.5 ሜትር ያላነሰና በሕፃናት ላይ አደጋን የማያስከትል መሆን አለበት፣
- አጥሩ እሾሃማ መሆን የለበትም፤

DRAFT

- ለጥላና ለመዝናኛ የሚያገለግሉ ዛፎች ሊኖሩት ይገባል፤
- ልዩ ልዩ የመጫወቻና የአካል ማጐልመሻ መሣሪያዎች ያሉት ሆኖ የመሬቱ ወለል ለሕፃናቱ ልዩ ልዩ የአካል እንቅስቃሴ የሚመችና የተስተካከለ መሆን አለበት።
- ድብብቆሽ የሚጫወቱበት ቦታ ፣ የአሸዋ ሣጥን፣ የአበባና የአትክልት ቦታዎች ያሉት ሆኖ ስለዕፅዋት፣ ስለዘር፣ ስለተክል ወዘተ. ለመማር የሚያስችል መሆን አለበት፣
- የምድረ ግቢና የሕንፃው አደረጃጀት ለልዩ ፍላጐት ተማሪዎች በሚመች መልኩ መደራጀት ይኖርበታል።
- የምድረ ግቢው ስፋት እንደ መማሪያው ክፍሉ ብዛት ከ500-3000 ካሬ ሜትር ያለው መሆን አለበት።
- በግቢው ውስጥ የሕንፃው ወይም የህንፃዎቹ አቀማመጥ  የውጭ መጫወቻዎች ዝግጅትን እንዳያውክ ሆኖ መሰራት አለበት።
- የትምህርት ቤቱ ድንበር የተከበረ እና ወሰኑ የሚታወቅ እንዲሁም የይዞታና ቦታ ማረጋገጫ ካርታ ያለው ፣

## 2.3 የመማሪያ ክፍሎች መጠን እና ብዛት

አንድ የቅድመ መደበኛ ትምህርት ተቋም እያንዳንዳቸው 7x8=56 ካ.ሜ የሆኑ ቢያንስ እስከ 3 ክፍሎች ሊኖሩት ይገባል። በእነዚህም ክፍሎች ውስጥ 3x30=90 ሕፃናት ሊያስተናግድ ይችላል። በአንድ ክፍል ውስጥ ለሚገኙ ሕፃናት አንድ መምህር/ት እና አንድ ረዳት መምህር/ት ያስፈልጋሉ። ይህም ማለት 3 ክፍሎች ላሉት አንድ ቅድመ መደበኛ ተቋም 3 መምህራንና 3 ረዳት መምህራን በድምሩ 6 ያስፈልጋሉ ማለት ነው።  በአንድ ክፍል ውስጥ ከ30 ሕፃናት በላይ ማስተናገድ የለበትም።የመምህር/ት ህፃን ጥምርታ 1ለ15 መሆን ይገባዋል።

## 2.4 የመማሪያ ክፍሎች አሰራር እና አደረጃጀት

- የሕፃናት መማሪያ ክፍሎች ሲሠሩ ለያንዳንዱ ሕፃን ከ1.55 ሜትር ካሬ ያላነሰ ቦታ እንዲኖር ታሳቢ ተደርጎ መሰራት ይኖርበታል፣
- የመማሪያ ክፍሉ በርና  መስኮቶች አቀማመጥ በህፃናቱ ጤና ላይ ችግር የማያስከትል መሆን አለበት ፣

DRAFT

- የመማሪያ ክፍሉ ደረጃዎች እንዳይኖሩት ወይም እንዳይበዙበት ተደርጎ መሰራት ይኖርበታል፣
- ክፍሉ የአካል ጉዳተኛ ህፃናትን ታሳቢ ተደርጎ መሰራት አለበት፣
- የክፍሉ መስኮቶቹ ሕፃናት ወደ ውጭ በሚገባ ማየት የሚያስችሏቸው፣በሩም ክብደት የሌለውና ሳይፈለግ እንዳይዘጋ ከግድግዳው ጋር የሚያያይዝ ማጣበቂያ ሊኖረው ይገባል፣
- የክፍሉ የውስጥም ሆነ የውጭ ግድግዳ (ከብሎኬት፣ ከሸክላ፣ ከጭቃ ወዘተ.) የተሰራ ሆኖ ከወለሉ ቢያንስ 1 ሜትር ከፍታ ድረስ ሻካራ ያልሆነና በሕፃናቱ አካላት ወይም እጅ ላይ ጉዳት የማያደርስ መሆን አለበት፣
- ህፃናት የሚቀመጡበት ወንበር ክብደቱ ቀላል  እና እንደየእድሜ  ደረጃቸው የተዘጋጀ መሆን ይኖርበታል፣
- የመቀመጫ ወንበራቸው አቀማመጥ በቀላሉ ከቦታ ወደ ቦታ ማንቀሳቀስ የሚቻል እና ህፃናት በቀላሉ ከአንዱ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ እንዲዘዋወሩ እና ከመምህራቸው ጋር በቀላሉ ለመገናኘት የሚያስችል መሆን ይኖርበታል፣
- የመማሪያ ክፍሉ/ሎች ወለል እንደአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ (ከሲሚንቶ፣ ከሸክላ፣ወዘተ) የተሰራ፣ ንፁህ፣የማያዳልጥ ቢቻል ምንጣፍ የለበሰ መሆን ይኖርበታል፣
- የመማሪያ ክፍሉ ጣሪያ ከቆርቆሮ የተሰራና ዝናብ/ፍሳሽ የማያስገባ መሆን አለበት፣
- የመማሪያ ክፍሎች ህፃናቱን ለተለያዩ አደጋዎች  የሚያጋልጡ መሆን የለባቸውም፣
- በክፍሉ ወስጥ የህፃናቱ እቃዎች ( ቦርሳ፣የውሀ መያዣ ላስቲክ፣ የምግብ እቃ…ወዘተ) ማስቀመጫ፣ መደርደሪያ ወይም መሰል እቃ መኖር ይኖርበታል፣
- የመማሪያ ክፍሎቹ በቂ ብርሃን እና አየር የሚያስገቡ መሆን አለባቸው።

## 2.5 የአገልግሎት መስጫ ክፍሎች

- የመፀዳጃ ቤቱ ጣራና ግድግዳ ያለው፣ በቂ አየርና ብርሃን የሚያስገባ፤ ወለሉን በቀላሉ ለማጽዳት የሚቻል፣ የጉድጓዱ ቀዳዳ በሕፃናቱ የዕድሜ መጠን የተሠራና መግጠሚያ ያለው፣ የእጅ መታጠቢያም አጠገቡ ያለው  መሆን አለበት፣
- ለአካል ጉዳተኛ ህፃናት የሚመች መፀዳጃ ቤት ሊኖረው ይገባል፣

- መፀዳጃ ቤቱ ለሴት እና ለወንድ የተለየ መሆን ይኖርበታል፣
- የመጸዳጃ ቤቱ ክፍሎች እንደ አካባቢው ሁኔታ ብርሃንን፤ ሙቀትን፤ ብርድን፤ ዝናብንና ትንኞችን ለመቆጣጠር በሚያስችሉ እንደ መስተዋትና እንዲሁም በሽቦና ከመሳሰሉት የተሠራ የወንፊት መስኮት ሊኖራቸው ይገባል።

ሰንጠረዥ 1:- በአፀደ ህጻናትሊኖሩ የሚገባቸው የአገልግሎት መስጫ ክፍሎች

| ተራ ቁጥር | የሕንፃው ክፍሎች | ባለ 1 ክፍል | ባለ 2 ክፍል | ባለ 3 ክፍል | ባለ 4 ክፍል | ባለ 5 ክፍል | ባለ 6 ክፍል | የአንድ ክፍል መጠን በካሬ ሜትር | መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የመማሪያ ክፍል | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7X8 | |
| 2 | ጽ/ቤት ቢሮ | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 4.2 X5 | |
| 3 | ዕቃ ግ/ቤት | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 2.8X2.5 | |
| 4 | የምሳ መያዣ እቃ ማስቀመጫ ቁም ሳጥን/ መደርደሪያ | 1 | 1 | 1 | 2 | 2 | 2 | 5X5 | |
| 5 | መመገቢያ ክፍል | 1 | 1 | 1 | 2 | 2 | 2 | 4X5 | |
| 6 | የምግብ ዕቃ ግምጃ ቤት | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 3.40X3.7 | ምግብ በሚዘጋጅበት አፀደ ህጻናት |
| 7 | የምግብ ማብሰያ | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 5X5.6 | ምግብ በሚዘጋጅበት አጸደ ህጻናት |
| 8 | የሕፃናት መፀዳጃና መታጠቢያ | 1 | 1 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2X1.5 | በፆታ የተለየ |
| 9 | የመምህራን እና ሰራተኞች መፀዳጃ (ለወንድ እና ለሴት ለየብቻ) | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 2X2.4 | |
| 10 | የሕፃናት ማረፊያ ክፍል | 1 | 1 | 1 | 2 | 2 | 2 | 4X5 | |
| 11 | ሁለገብ አዳራሽ | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 8X14.1 | |
| 12 | የጥበቃቤት | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 2.45X2.45 | |
| 13 | የገ/ያዥ ቢሮ | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 3X2 | |
| 14 | የመምህራን ማረፊያ | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 3X7 | |
| 15 | የመጀመሪያ ሕክምና ዕርዳታ መስጫ | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 2.5X3 | |
| 16 | የጽዳት ዕቃ ማስቀመጫ | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 2.5X2 | |

| ተራ ቁጥር | የሕንፃው ክፍሎች | ባለ 1 ክፍል | ባለ 2 ክፍል | ባለ 3 ክፍል | ባለ 4 ክፍል | ባለ 5 ክፍል | ባለ 6 ክፍል | የአንድ ክፍል መጠን በካሬ ሜትር | መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 17 | የስፖርት መስሪያ ሜዳ | 1 | | | | | | 10X10 | |
| 18 | የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ቅርጫት ወይም ፕላስቲክ | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | | ከክፍል ውጭ ቢያንስ 3 የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ቅርጫት ያስፈልጋል። |
| 19 | የንግግር/አንደበት ወጌሻ መስጫ ክፍል | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 3X3 | እንዳስፈላጊነቱ |
| 20 | የትምህርት ማበልጸጊያ ማዕከል | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 4X5 | |
| 21 | የሚጥል ችግር (Epilepsy) ላለባቸው ልጆች ችግሩ ሲፈጠር ማሳረፊያ ክፍል ፍራሾች የተነጠፉበትና አየር በደንብ የሚያስገባ | | | | | | | | የመጀመሪያ ሕክምና ዕርዳታ መስጫ ክፍልን መጠቀም ይቻላል። |

## 2.6 ለልዩ ልዩ ክፍሎች አስፈላጊ መሣሪያዎች

ሰንጠረዥ 2:- ለአንድ መማሪያ ክፍል የሚያስፈልጉ ቋሚ መሣሪያዎች፣

| ተራ ቁ. | የዕቃው ዓይነት | ብዛት | መጠን በሳ/ሜ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ጥቁር/ ነጭ ሠሌዳ | 1 | 50 X 100 | |
| 3 | ሰሌዳ ማጥፊያ | 2 | - | |
| 4 | የማስታወቂያ መለጠፊያ ሰሌዳ | 1 | 50 X 100 | |
| 5 | የመምህር/ት ወንበር | 1 | 40 X 56 X 78 | |
| 6 | የመምህር/ት ጠረጴዛ | 1 | 80 X 100 X 74 | |
| 7 | የሕፃናት ወንበሮች | 30 | 34 X 24 X 27 | |
| 8 | የሕፃናት ጠረጴዛዎች | 10 | 68 X 98 X 75 | |
| 9 | ዕቃ መደርደሪያዎች | 3 | 10 X 200 X 40 | |
| 10 | የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ቅርጫት | 1 | | ከሳጠራ/ከፕላስቲክ የተሠራ |

- በክፍል ውስጥ ለትምህርት የሚያገለግሉ ቁሳቁሶች ክብደት፣ ቁመት… ወዘተ የህጻናቱን እድሜ እና ተክለ ሰውነት እና ብዛት ከግምት ውስጥ ያስገቡ መሆን ይኖርባቸዋል።

- ቁሳቁሶቹ ተፈጥሯዊ ከሆኑ ነገሮች የተሰሩ፣ ቀላልና በጤንነታቸው ላይ እክል የማያመጡ መሆን ይኖርባቸዋል።

ሰንጠረዥ 3:- ከህፃናት ተማሪዎች ጋር የተያያዙ መረጃዎች

| ተራ ቁ. | የመረጃ አይነት | መግለጫ |
|---|---|---|
| 1 | በት/ቤቱ ያሉ ህፃናት አጠቃላይ መረጃ | |
| 2 | የተማሪዎች ስም መቆጣጠሪያ | |
| 3 | የእንግዶች አስተያየት መቀበያ መዝገብ/ደብተር | |
| 4 | የተከታታይ ምዘና ውጤት ሪፖርቶች | |
| 5 | የህጻናት የግል ማህደረ ተግባር | |

ሰንጠረዥ 4:- የመማሪያ መፃህፍት በአይነትና በምጣኔ፣

| ተራ ቁ. | የመፅሀፉ ዓይነት | ምጣኔ | መግለጫ |
|---|---|---|---|
| 1 | የህፃናት መማሪያ/መለማመጃ ደብተር | 1ለ1 | |
| 2 | አጋዥ መፃህፍት | 5ለ1 | |
| 3 | ለልዩ ፍላጎት | 1ለ1 | |

ልዩ የመማር ፍላጐት ላላቸው ሕፃናትበተጨማሪ የሚከተሉት መሣሪያዎች ያስፈልጋሉ።

**መስማት ለተሳናቸው ሕፃናት**

- መሣሪያዎች መንቀሳቀሳቸውን የሚያመለክት ብርሃን ማሳያ፣
- የማስጠንቀቂያ ደወል ለመተካት እንደባትሪ ያሉ ነገሮች እንዲታይ ማድረጊያ፣
- በከፊል ለሚሰሙት ድምፅ ማጉያ መሣሪያ መጠቀም ለምሳሌ፡-ረዳት የመስሚያ መሣሪያ፣
- ድምፅ - አልባ የታይፕ መኪና መጠቀም፣
- የዕይታ መሣሪያዎች ብርሃን አስተላላፊ ወረቀት፣ፊልም፣ ስላይድ፣ፊልም፣ ቻርት መስሪያ

**ለአይነ ስውራን ህፃናት**

- አባከስ
- ብሬል
- ስሌት
- ስታይለስ

- ዘንግ
- ቴፕሪከርደር
- በኮምፒውተር ላይ የተጫነ የጃውስ ፕሮግራም

**የአእምሮ ዕድገት ውስኑነት ላለባቸው ህፃናት**

- ቴሌቪዥን
- ዲቪዲ ማጫወቻ
- የፊዚዮቴራፒ ኳሶች
- ሞንቶሶሪ ኪትስ

**ለተግባራዊ ትምህርት የሚያገለግሉ መሣሪያዎች**

**ለቅድመ መደበኛ ትምህርት ፕሮግራም የተዘጋጁት መሣሪያዎች ልዩ ፍላጐት ላላቸው ሕፃናትም ጭምር ያገለግላሉ።**

ሰንጠረዥ 5:- የመጀመሪያ ደረጃ ሕክምና ዕርዳታ መስጫ ዕቃዎች በአይነትና በብዛት

| ተራ ቁጥር | የዕቃው ዓይነት | ብዛት |
|---|---|---|
| 1 | የጥጥ ዕቃ | * |
| 2 | ሶስት መዓዘን ፋሻዎች | * |
| 3 | ጥቅል ፋሻዎች | * |
| 4 | የተቀቀሉ የጨርቅ ፓዶች | * |
| 5 | የተቆራረጡ በራዚዎች | * |
| 6 | ከፋሻ ጋር የተያያዙ ፓዶች | * |
| 7 | የላስቲክ ፋሻ | * |
| 8 | የእጅ ፎጣ | * |
| 9 | የተጎዳ አካልን ለማሰር የምንጠቀምበት እንጨት /ስፕሊንት/ | * |
| 10 | የሕፃናት መመርመሪያ አልጋ | 1 |
| 11 | ፍራሽ | 1 |
| 12 | ብርድ ልብስ | 2 |
| 13 | አንሶላ | 4 |
| 14 | የመድኃኒት ስኒ | 2 |
| 15 | መቀስ | 2 |
| 16 | ወረንጦ | 2 |
| 17 | መርፌ ቁልፎች | እንደተገኘ |
| 18 | የቁስል መለጠፊያ ፕላስተር | " |
| 19 | ማስታወሻ ደብተር | " |
| 20 | ሳሙና ከነመቀመጫው | " |
| 21 | የመጠጫ ኩባያ | 2 |
| 22 | ትንሽ ሳህን | 2 |

DRAFT

**ማሳሰቢያ፣**

* ከላይ ከተዘረዘሩት መካከል በቁጥር ላልተገለጹ ህክምና ዕርዳታ መስጫ/ዕቃዎችን ብዛት እንደ ሕፃናቱ ብዛት ግምት ውስጥ ያስገባ መጠን መሆን አለበት።

ሰንጠረዥ 6:- ለመጀመሪያ ሕክምና ዕርዳታ መስጫ ክፍል የሚያስፈልጉ መድኃኒቶች

| ተራ ቁ. | የመድኃኒቱ ዓይነት | ብዛት |
|---|---|---|
| 1 | የሕፃናት አስፕሪን | እንደተገኘ |
| 2 | ቴምፕራ ሲረፕ/ፈሳሽ/ | " |
| 3 | የሳል ማስወገጃ መድኃኒት | " |
| 4 | የተቅማጥ መቆጣጠሪያ መድኃኒት | " |
| 5 | ቴትራሳይክሊን የዓይን ቅባት | " |
| 6 | ፕላሲል ፈሳሽ | " |
| 7 | አዮዲን | " |
| 8 | ጀንሺያን ባዩዋሌት | " |
| 9 | አልኮል | " |
| 10 | ሳልፋ ዱቄት ወይም ቅባት | " |
| 11 | ቤንዚን ኮኒየም (የቁስል ማጠቢያ) | " |
| 12 | ባለመድኀኒት ፕላስተር | " |

**ማሳሰቢያ፣**

ከላይ የተዘረዘሩ ለመጀመሪያ ሕክምና ዕርዳታ መስጫ የሚያስፈልጉ መድኃኒቶች ብዛት በተቋሙ በሚማሩ ሕፃናት ቁጥር ተመጣጣኝ መሆን አለበት።

ሰንጠረዥ 7:- ለማዕድ ቤት የሚያስፈልጉ ዕቃዎች በአይነትና በብዛት

| ተራ ቁጥር | የዕቃው ዓይነት | ብዛት | መግለጫ |
|---|---|---|---|
| 1 | ማንቆርቆሪያ | 1 | |
| 2 | ብረት ድስት | 1 | |
| 3 | የሸክላ ድስት | 2 | |
| 4 | ማቡኪያ ሣህን ወይም ገበቴ | 4 | ለዳቦ እና ለእንጀራ |
| 5 | ባልዲዎች | 4 | |
| 6 | የዕቃ መደርደሪያ | 1 | |
| 7 | ማብሰያ ምድጃ | 1 | |
| 8 | ትናንሽ ማንኪያዎች | በተማሪ ቁጥር | |
| 9 | ትናንሽ ማብሰያ ሣህኖች | ″ | |
| 10 | የሻይ፣የውሃና የወተት ኩባያ | ″ | |
| 11 | የዳቦ ማቅረቢያ ትሪ | 5 | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 12 | ጭልፋዎች | 3 | |
| 13 | ወንፊትና ሰፌድ | 2 | |
| 14 | ቢላዎች | 5 | |
| 15 | መጥበሻዎች | 2 | |
| 16 | የዕቃ መወልወያ ንጹህ ጨርቆች ባለ 1 ሜትር | 5 | |

ሰንጠረዥ8 :- የትምህርት እና የጨዋታ ማዕዘኖች በአይነትና በብዛት

| ተራ ቁ. | የዕቃው ዓይነት | ብዛት | የተሠራበት ማቴሪያል |
|---|---|---|---|
| 1 | ለቤተሰብ ማዕዘን የሚያስፈልጉ | | |
| | ▪ ስኒዎች | እንደተገኘ | |
| | ▪ ጀበናዎች | >> | ከሸክላ፣ከብረት |
| | ▪ ማንኪያዎች | >> | ከሸክላ፣ከብረት |
| | ▪ ሣህኖች | >> | ከሸክላ፣ከፕላስቲክ፣ |
| | ▪ አሻንጉሊቶቸ | >> | ከጨርቅ፣ፕላስቲክ |
| | ▪ ትናንሽ የአሻንጉሊት አልጋዎች | >> | ከእንጨት፣ከፕላስቲክ |
| 2 | ለሕክምና/ለጤናማዕዘን የሚያስፈለጉ | | |
| | ▪ ሽርጦች | 4 | ከጨርቅ |
| | ▪ ስሪንጆች | እንደተገኘ | ከጎማ፣ፕላስቲክ |
| | ▪ ማዳመጫዎች | “>> | ከዕንጨት |
| | ▪ ፋሻዎች | 4 | ከጨርቅ |
| | ▪ የመድኃኒት ብልቃጦች | እንደተገኘ | ከፕላስቲክ፣ከጠርሙስ |
| | ▪ እንደ ስትሬቸር የሚያገለግሉ አልጋዎች | >> | ከሣጠራ፣ከእንጨት |
| 3 | ለሱቅ ማዕዘን የሚያስፈልጉ | | ከፕላስቲክና ከብረት |
| | ▪ ሚዛን | እንደተገኘ | ከፕላስቲክ፣ከብረት |
| | ▪ ባዶ የእስክሪቢቶ ቀፎዎች | >> | ከፕላስቲክ |
| | ▪ ባዶ የክብሪት ቤቶች | >> | ከእንጨት |
| | ▪ የተለያዩ የሕፃናት ልብሶች | >> | ከጨርቅ |
| | ▪ ቆርኪዎች | >> | ከቆርቆሮ |
| | ▪ ልዩ ልዩ የቤት ቁሳቁሶች | >> | ከአፈር፣ከሲሚንቶ |
| | ▪ የገንዘብ ኖቶችና ሳንቲሞች | >> | ከወረቀት፣ከፕላስቲክ |
| 4 | ለሳይንስ ማዕዘን<br>▪ ልዩ ልዩ የሳይንስ ኪቶች | >><br>>> | ከወረቀት፣ ከፕላስቲክ<br>ከወረቀት፣ከዕንጨት፣ ከጭቃ፣ወዘተ |
| 5 | ለኅብረተሰብ ማዕዘን<br>▪ ልዩ ልዩ ሥዕሎችና የአካባቢ አልባሳት | >><br>>> | ከጨርቅ፣ ወረቀት፣ጭቃ |
| 6 | ለቋንቋና የንባብ ማዕዘን<br>▪ ሥዕሎች፣ጋዜጦችና የሕፃናት መፃሕፍት | እንደተገኘ | |

DRAFT

| ተራ ቁ. | የዕቃው ዓይነት | ብዛት | የተሠራበት ማቴሪያል |
|---|---|---|---|
| 7 | ለሂሣብ ማዕዘን<br>▪ ልዩ ልዩ ቁጥሮች መቁጠሪያ መማሪያዎችና ምልክቶች<br>▪ አባከስ | >> | ከፕላስቲክና ከእንጨት፣ከወረቀት ከጭቃ |
| 8 | ለሙዚቃ ማዕዘን<br>▪ የሙዚቃ መሳሪያዎች<br>▪ ልዩ ልዩ የአካባቢና ባህላዊ መሣሪያዎች | >><br>>> | ከዕንጨት፣ከቆዳ፣ከጅማት ክር |
| 9 | ለሥነ ሥዕል ማዕዘን<br>▪ የተለያዩ ስዕሎች፣ ቅርፃቅርፆች | | ከጨርቅ፣ከእንጨትና ከሸክላ፣ ከጠንካራ ወረቀት/ክላሰር/፣ |
| 10 | ለስፖርት ማዕዘን | | |
| 11 | ለግንባታ ማዕዘን | | |
| | ▪ የመገንቢያ ብሎኮች | እንደተገኘ | ከሸክላ፣ፕላስቲክ፣እንጨት |

ከላይ የቀረቡት ማዕዘኖች በአምስት ዋና ዋና ማዕዘኖች ማለትም በሂሳብ፣ በግንባታ፣ በቋንቋ፣ በሳይንስ እና በስነጥበብ /በሙዚቃ ጥንች ስር መመደብ ይኖርባቸዋል።እንዲሁም ከላይ የተዘረዘሩት የመማሪያ እና የመጫዎቻ መሣሪያዎች እንዲሁም በመምህራን ከአካባቢ በሚገኙ ቁሳቁሶች ተዘጋጅተው ስራ ላይ የሚውሉ ቁሶች የህፃናቱን አቅም ያገናዘቡ፣ እያዝናኑ እና እያስደሰቱ ሊያስተምሩ የሚችሉ እና በህፃናት ላይ ምንም አይነት ጉዳት የማያደርሱ መሆናቸው መረጋገጥ ይኖርበታል።

ሰንጠረዥ 9:- ቋሚ የውጭ መጫወቻ መሣሪያዎች በአይነትና በብዛት

| ተራ ቁ. | የዕቃው ዓይነት | ብዛት | ምርመራ |
|---|---|---|---|
| 1 | ኳሶች | 5 ኳስ ለ30 ሕፃናት | 1 ኳስ ለ6 ሕፃናት |
| 2 | ጐማዎች | 10 | |
| 3 | ኀ 
ዋኀ 
ዌ | 2 | |
| 4 | ሚዛን | 2 | |
| 5 | ሸርተቴ | 2 | |
| 6 | ሜራጎራውንድ | 2 | |
| 7 | መሰላል | 2 | |
| 8 | የመሹለኪያ ቱቦዎች | 2 | |
| 9 | የአሸዋ ሣጥን | 2 | |
| 10 | ገመድ | 10 | |

DRAFT

ማሳሰቢያ፣

ለልዩ ፍላጎት እና ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች የሚሆኑ አማራጭ የመጫወቻ መሳሪያዎች ሊቀርቡላቸው ይገባል።

ከላይ የተገለፀው እያንዳንዱ የዕቃ ዓይነት ብዛት ለ30 ሕፃናት ሲሆን የሕፃናቱ ቁጥር በጨመረ ቁጥር የዕቃዎቹም ብዛት እንደሚጨምር ይጠበቃል።

ሰንጠረዥ 10:- ለርዕሰ መምህርት/ር ቢሮ የሚያስፈልጉ ዕቃዎች

| ተራ ቁጥር | የዕቃው ዓይነት | ብዛት | ዓይነት |
|---|---|---|---|
| 1 | ወንበር | 4 | |
| 2 | ባለኪስ ጠረጴዛ | 1 | |
| 3 | የመፀሐፍ መደርደሪያ | 1 | |
| 4 | የማስታወቂያ መለጠፊያ ሰሌዳ | 1 | ከሳጠራ/ከፕላስቲክ የተሠራ |
| 5 | የቆሻሻ ማጠራቀሚያ | 1 | |
| 6 | የእርሳስ መቅረጫ | 1 | |
| 7 | ስቴፕለር | 1 | |
| 8 | ማስመሪያ | 1 | |
| 9 | መዛግብት | እንደአስፈላጊነት | |
| 10 | የፋይል አቃፊዎች | " | |
| 11 | ወረቀት | " | |
| 12 | ክላስር | " | |
| 13 | የወረቀት መርፌ | " | |
| 14 | ካርቦን | " | |

# ክፍል ሶስት

## 3. የሰው ኃይል ምደባ

### 3.1 የመምህራንና ሠራተኞች ድልድል፤

- የቅድመ መደበኛ ተቋም ርዕሳነ መምህራን፤ መምህራንና ሞግዚቶች ሴቶች ቢሆኑ ይመረጣል፣
- አንድ መምህር/ት 30 ሕፃናትን ያስተናግዳል/ታስተናግዳለች፣
- 30 ሕፃናትን ለምታስተምር መምህር/ት አንድ ረዳት መምህር/ት ትመደባለች፣

  አንድ ሞግዚት ለ 30 ሕፃናት ትመደባለች፣
- ለአንድ ቅድመ መደበኛ ትምህርት ተቋም እንደ ክፍሎችና ሕፃናቱ ብዛት የሰው ሀይል ይመደባል።
- አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ባሉበት ክፍል እንደተማሪዎቹ የአካል ጉዳት አይነት ተጨማሪ መምህር/ት መመደብ ይኖርበታል/ባታል።

ሰንጠረዥ 11:- የመምህራንና ሠራተኞች ብዛት

| የመማሪያ ክፍል | የሕፃናት ብዛት | የር/መምህር/ት ብዛት | የመምህራንብዛት | የረዳት መምህራንብዛት | የሞግዚትብዛት | የጥበቃ ሠራተኞች | ተላላኪ ብዛት | የጽዳት ሠራተኞች ብዛት | የጤና ባለሙያ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ባለ 1 መማሪያ ክፍል | 30 | 1 | 1 | 1 | 1 | 2 | 1 | 1 | 1 |
| ባለ 2 መማሪያ ክፍል | 60 | 1 | 2 | 2 | 2 | 2 | 1 | 1 | 1 |
| ባለ 3 መማሪያ ክፍል | 90 | 1 | 3 | 3 | 3 | 2 | 1 | 1 | 1 |
| ባለ 4 መማሪያ ክፍል | 120 | 1 | 4 | 4 | 4 | 2 | 1 | 2 | 1 |
| ባለ 5 መማሪያ ክፍል | 150 | 1 | 5 | 5 | 5 | 2 | 1 | 2 | 1 |
| ባለ 6 መማሪያ ክፍል | 180 | 1 | 6 | 6 | 6 | 2 | 1 | 2 | 1 |

**ማሳሰቢያ፣**

**የህፃናቱ ቁጥር በጨመረ ቁጥር የሰው ኃይል ምደባው በተገለጸው ሥሌት መሠረት የሚጨምር ይሆናል።**

DRAFT

ከአንድ እስከ ሁለት መማሪያ ክፍሎች ላላቸው ቅድመ መደበኛ ትምህርት ተቋማት በሥራ ልምድና በአገልግሎት ዘመን ብልጫና በሥራ ትጋት የተሻለ/ች አንድ/ዷት መምህር/ት ከማስተማር ሥራው/ዋ በተጨማሪ የቅድመ መደበኛ ትምህርት ተቋም ኃላፊ መምህር በመሆን ያገለግላል/ ታገለግላለች። ነገር ግን ከሁለት የመማሪያ ክፍል በላይ ላላቸው ትምህርት ተቋማት ራሱን የቻለ ኃላፊ መመደብ ይኖርበታል።

## 3.2 የመምህራንና የሠራተኞች የትምህርት ደረጃ፣

ሰንጠረዥ 12:- ቅድመ መደበኛ ትምህርት መምህራንና ሰራተኞች የትምህርት ደረጃና ብዛት

| ተራ ቁ. | የሠራተኛው ሙያ ዓይነት | የትምህርት ደረጃ | መግለጫ |
|---|---|---|---|
| 1 | ርዕሰ መምህር/ት | በቅድመ መደበኛ ትምህርት ዲፕሎማ ያላት/ው እና ድህረ ምረቃ ሰርተፍኬት ያላት/ | |
| 2 | መምህር/ት | በቅድመ መደበኛ ትምህርት መምህርነት ዲፕሎማ | |
| 3 | ረዳት መምህር/ት | በቅድመ መደበኛ ትምህርት መምህርነት ዲፕሎማ | |
| 4 | የልዩ ፍላጎት መምህራን | በቅድመ መደበኛ ትምህርት ዲፕሎማ ያለው/ት እና በልዩ ፍላጎት ትምህርት አጫጭር ሥልጠናዎች የወሰደ/ች | እንደ ህፃናቱ ብዛት |
| 5 | ሞግዚት | 10ኛ ክፍልን ያጠናቀቀች ሆኖ ቢቻል በሥርዓተ ምግብ ሥልጠናና በምግብ ዝግጅት ልምድ ያላት፣ | |
| 6 | ጥበቃ/አትክልተኛ | 8ኛ ክፍል ያጠናቀቀ/ች | |
| 7 | የፅዳት ሠራተኛ | 8ኛ ክፍል ያጠናቀቀ/ች | |
| 8 | ንብረት ክፍል ሀላፊ | በንብረት አያያዝ ደረጃ 2 የተመረቀች | |

**ማሳሰቢያ:-**

- በልዩ ፍላጎት ትምህርት የሰለጠኑ መምህራን የሚያስፈልጉት ልዩ የመማር ፍላጎት ያላቸው ሕፃናት ባሉበት የቅድመ መደበኛ ትምህርት ተቋም ነው።

DRAFT

# ክፍል አራት

## 4.1 የቅድመ መደበኛ ትምህርት መርሀ ግብር ፕሮግራም

*የቅድመ - መደበኛ ትምህርት መርሀ ግብር ዕድሜያቸው ከ4-6 ዓመት የሆናቸውን ልዩ የመማር ፍላጐት ያላቸው ሕፃናትን ጨምሮ ሁሉም ህጻናት ሁለገብ የሆነና ለዘላቂ ሕይወታቸው መሠረት የሚጥል ዕውቀት፤ ክህሎትና አዎንታዊ ባህርይ እንዲያገኙ ለማድረግ የተዘረጋ የትምህርት እርከን ነው።*

*በዚህ ደረጃ ሕፃናት ከማንኛውም የትምህርት እርከን በበለጠ ጥበቃና እንክብካቤ ተደርጎላቸው፤ በአካል፣ በአእምሮ፣ በስሜትና በማኅበራዊ ኑሮ ተገቢውን የዕድገት መሠረት አግኝተው ማደግ እንዲችሉ አስፈላጊውን ሁሉ ማድረግ ይገባል። ይህም የወላጆችንና የኅብረተሰቡን የቅርብ ክትትል፤ የመምህራንን ትጋትና ከፍተኛ ጥረት እንዲሁም፤ የመንግሥትን ትኩረት የሚጠይቅ ነው።መርሀ ግብሩን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያግዝ አደረጃጀት፤አመራርና አስተዳደር፣ የፖሊሲ ማዕቀፍ፣ መመሪያዎች ፣የስርአተ ትምህርት መሳሪያዎች እንዲሁም ልዩ ልዩ ማስተግበሪያ ሰነዶች በስራ ላይ የሚገኙ ሲሆን ሀገራዊና አለምአቀፋዊ ሁኔታዎችን እና አዳዲስ አስተሳሰቦችን መሰረት በማድረግ እና የሀገሪቷን የወደፊት እድገትና ልማት ታሳቢ በማድረግ ለወደፊቱ መርሀ ግብሩ የተሻለ ደረጃ የሚደርስበት ሁኔታዎች ይመቻቻሉ ። ስለሆነም መመሪያዎቹ በየደረጃው ባሉ ኃላፊዎች፣ ተጠቃሚ ክፍሎችና ሌሎች ባለድርሻ አካላትን ጨምሮ በሁሉም ዘንድ ታውቀውና ተመጣጣኝ ግንዛቤ ተፈጥሮባቸው ስለአፈጻጸማቸው ክትትልና ቁጥጥር እየተደረገና አስፈላጊው ሙያዊ ድጋፍ እየተሰጠ ሥራ ላይ እንዲውሉ ማድረግ ያስፈልጋል።*

## 4.2 የፕሮግራሙ አወቃቀር/አደረጃጀት

*የቅድመ መደበኛ ትምህርት ፕሮግራም (መርሀ ግብር) ከ4 – 6 ዓመት የዕድሜ ክልል ውስጥ ለሚገኙ ሁሉም ህፃናት ደረጃውን ጠብቆ ለሶስት ዓመት የሚካሄድ ፕሮግራም ነው።በመሆኑም የህፃናቱን እድሜ መሰረት በማድረግ መርሀ ግብሩ በደረጃ አንድ ለ4 አመት፣በደረጃ ሁለት ለ5 አመት እንዲሁም በደረጃ ሶስት ለ6 አመት ህፃናት ይሰጣል።ፕሮግራሙ ልዩ ፍላጎት ያላቸዉን ህፃናትም የሚያካትት ሲሆን በዋናነት የሚከተሉትን ያጠቃልላል።*

- *ለአይነ ስውራን፣*
- *መስማት ለተሳናቸው፣*
- *የአእምሮ ዕድገት ውስንነት ላለባቸው፣*

- በአካላዊ ጉዳት ምክንያት ከቦታ ወደ ቦታ መንቀሳቀስ የሚያዳግታቸው፣
- ከሌሎች ጋር የመግባባት / የመናገር ተግዳሮት ላለባቸው፣
- የባህርይ እና ማህበራዊ ተግባቦት እክል ላለባቸው፣
- የመማርና የማንበብ እክል ላለባቸው፣
- የመማር እክል ያለባቸው፣
- የመናገር ችግር ያለባቸው፣
- የአካል ላይ ጉዳት (Physical or Orthopedic Impairment) ያለባቸው፣
- የሚጥል በሽታ ያለባቸው፣
- ኦቲስቲክ የሆኑ ልጆች፣
- ተደራራቢ የአካል ጉዳት ላለባቸው፣
- የስሜት መረበሽ ያለባቸው፣
- ልዩ ተሰጥኦ ያላቸው....ወዘተ ናቸው።

## 4.3 የቅድመ መደበኛ ትምህርት መርሀ ግብር የትኩረት አቅጣጫዎች

በቅድመ መደበኛ ትምህርት የሚካሄደው ፕሮግራም ተግባራዊ የሚሆነው /ማስተላለፊያ ዘዴው/ (method) በነፃ እና በታቀደ ጨዋታ ነው። ይህ የማስተማሪያ ዘዴ የተመረጠበት ምክንያት በዚህ ዕድሜ ክልል ያሉ ህፃናት ጨዋታን እንደ ዋና ተግባራቸው አድርገው ስለሚወስዱትና ጨዋታ የህፃናትን አካል በማዳበር፣ አእምሯቸውን በማበልጸግ፣ እንዲሁም ማህበራዊና ስሜታዊ እሴቶቻቸው በማጎልበት ረገድ የጎላ ፋይዳ ስላለው ነው። ስለሆነም ሕፃናት የአካል፣ የመንፈስ፤ የስሜትና የማህበራዊ ኑሮ አስተሳሰብ ብቃታቸው ዳብሮ ለመደበኛው ትምህርት ዝግጁ የሚሆኑት በግልና በጋራ በሚካሄድ ጨዋታ በመሆኑ ለጨዋታው የተለየ ትኩረት መሰጠት ይገባል።

## 4.4 የቅድመ መደበኛ ትምህርት አቀራረብ

ለሶስት አመት የሚሰጠው የቅድመ መደበኛ ትምህርት መርሀ ግብር የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ በ3 ዋና ዋና ተግባራት ላይ ያተኩራል።

እነዚህም፣

### 4.4.1 ነፃና የታቀደ ጨዋታ፣

- በሕፃናቱ ምርጫ የሚከናወኑ ጨዋታዎች፤
- በመምህራን መሪነት የሚከናወኑ ጨዋታዎች፤
- አካል ጉዳት ያለባቸው ልጆች ጉዳት አልባ ከሆኑ አኩዮቻቸው ጋር የሚጫወቷቸው ጨዋታዎች

### 4.4.2 በክፍልና ከክፍል ውጭ ተቀናጅተው የሚሰጡ የትምህርት አይነቶች

- ቋንቋ (የአፍ መፍቻ ቋንቋ)
- የአካባቢ ሣይንስ ትምህርት
- ሂሣብ
- ሥዕል፣ሙዚቃና የሰውነት ማጐልመሻ
- እንግሊዘኛ

### 4.4.3 ግላዊና ማህበራዊ ጠቀሜታ ያለው ሥራዎች

ህፃናት የሚያከናውኗቸው ሥራዎች በሁለት ይከፈላሉ። እነዚህም፡-

- ግላዊ ጠቀሜታ የሚሰጡ ሥራዎች እና
- ማኀበራዊ ጠቀሜታ የሚሰጡ ሥራዎች ናቸው።

4.5 ከላይ ከተጠቀሱት የጨዋታ፣የትምህርት እና ግላዊና ማህበራዊ ጠቀሜታ ካላቸው ሥራዎች በተጨማሪ ልዩ ፍላጎት ላላቸው ሕፃናት የሚከተሉት ተግባራት ሊመቻቹላቸው ይገባል።

### 4.5.1ለአይነ ስውራን

- የስሜት ሕዋሳትን የማነቃቃትና የማዳበር፣
- የነፃ እንቅስቃሴ ትውውቅ/ሞብሊቲና ኦረንቴሽን ልምምድ፣
- የዕለት ተዕለት አኗኗር ክሂልን የማዳበር፣
- ቅድመ-ብሬል ዝግጁነት፣
- ቅድመ-አባከስ ዝግጁነት፣
- የእይታ ስሜት ቀስቃሽ ክንውን /በመስማት እንዲያዳብሩ/ ፣
- ከአንድ በላይ የመማሪያ ዘዴን ማዳበር፣
- የማዳመጥ ልምምድ፣
- በአደጋ ጊዜ ጆሮን በመጠቀም አካባቢን ስለመረዳትእና የመሳሰሉትን ያካትታል።

DRAFT

### 4.5.2 መስማት ለተሳናቸው

- ከናፍረ-ንባብ፣
- የማዳመጥ ልምድ (በከፊል መስማት ለሚችሉ)
- መስማት ለሚያከራክራቸው የንግግር ልምምድ፣
- የጣት ፊደል ቆጠራ ልምምድ፣
- የምልክት ቋንቋ ልምምድ፣
- የቋንቋ ልምምድ፣
- ስለ ረዳት መስሚያ መሣሪያዎች የአጠቃቀም ልምምድ፣
- በአደጋ ጊዜ ዓይንን በመጠቀም አካባቢን ስለመረዳት እና የመሳሰሉትን ያካትታል።

### 4.5.3 የአእምሮ ዕድገት ውስንነት ላለባቸው

- የአካልእንቅስቃሴ፣
- እጅን እንደተፈለገ የመጠቀም ልምምድ፣
- ጨዋታ፣
- ንግግር እና ቋንቋን የማዳበር ክሂል፣
- ማኅበራዊ ክሂሎችን ማዳበር፣
- የግል ንፅህናና ጤንነትን  መጠበቅ፣
- ራስን የመርዳት ክሂሎች፣
- ራስን መምራት፣
- ሥነጥበብና ሙዚቃ፣
- ቅርፆችንና ቀለሞችን መለየት እና
- ከአደጋ መጠበቅ (የመኪና መንገድ ማቋረጥ፤ እሳት ፤ ኤሌክትሪክ ወዘተ ከመሳሰሰሉ አደጋዎች ስለመጠበቅ) እና የመሳሰሉትን ያካትታል።

DRAFT

### 4.5.4 አካላዊ ጉዳት ችግር ላለባቸው

- *የስሜት ሕዋሳትን የማነቃቃትና የማዳበር፣*
- *የአካል እንቅስቃሴ ልምምድ፣*
- *ራስን የመርዳት ክሂሎች ልምምድ፣*
- *የዕለት ተዕለት የህይወት ክሂል የማዳበር ልምምዶችን እና የመሳሰሉትን ያካትታል።*

### 4.5.5 ከሌሎች ጋር የመግባባት / የመናገር/ ችግር ላለባቸው

- *የፊደላት እና የቃላት አወጣጥ ልምምድ፣*
- *የቋንቋ/ ንግግር ልምምድ፣*
- *የስሜት ሕዋሳትን የማነቃቃትና የማዳበር ልምምዶችን እና የመሳሰሉትን ያካትታል።*

### 4.5.6 የባህርይ እና ማህበራዊ ችግር ላለባቸው

- *ማህበራዊ ክሂልን ማዳበር፣*

### 4.5.7 የመማርና የማንበብ ችግር ላለባቸው

- *የፊደላት እና የቃላት አወጣጥ ልምምድ፣*
- *የቁጥሮች አፃፃፍ ልምምድ፣*
- *የፊደል አፃፃፍ/አጣጣል ልምምዶችን እና የመሳሰሉትን ያካትታል።*

### 4.5.8 የመማር ችግር ላለባቸው፣

- *ጨዋታቸውን ካለባቸው የመማማር ችግር አንጻር ማደራጀት፣*
- *ፊደላትን ለመጻፍ እርሳስን አስተካክሎ ስለመያዝ፣*
- *ፊደላትን ለመፃፍ ከግራ መጀመር፣*
- *መስመርን ጠብቆ ፊደላትን መፃፍና ማንበብ፣*
- *በትህትና የ□ደኛን ድጋፍ ስለመጠየቅ፣*
- *የመምህራን የወላጅን ትዕዛዝ ስለመረዳት፣*

### 4.5.9 የመናገር ችግር ላለባቸው፣

- *መዝሙሮችን ቃላት ሳይሸራርፉና ሳይተካኩ በትክክል ማስዘመር፣*
- *ያስቸገሯቸው ፊደላትን በተለያዩ ቃላት ውስጥ በማስገባት እንዲደጋግሙት ማድረግ*
- *የቋንቋ ልምምድ፣*

- ሥነጥበብና ሙዚቃ፣

### 4.5.10 የአካል ጉዳት (Physical or Orthopedic Impairment) ላለባቸው

- ሥነጥበብና ሙዚቃ፣
- በአቅማቸው የተዘጋጁ አካላዊ እንቅስቃሴዎች፣
- ሰው ሰራሽ የአካል ድጋፍ አጠቃቀምና በንፅህና ስለመያዝ፣
- የመፀዳጃ ቤት አጠቃቀም፣
- ሚዛንን ጠብቆ መራመድ፣ መዝለል እና መንከባለል፣
- ሳይወድቁ ትናንሽ የመጫወቻ ዕቃዎችን ማንቀሳቀስ፣
- አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የቴራፒ አገልግሎቶች እና የመሳሰሉትን ያካትታል።

### 4.5.11 የሚጥል ችግር ላለባቸው

- ጉዳት አልባ ህጻናት የሚማሩበትን መንገድ ተከትለን በተጨማሪነት የሚጥለው ችግር ከመከሰቱ ሰከንዶች ወይም ደቂቃዎች በፊት የሚሰማቸውን ያልተለመደ ስሜት እንዲያውቁ እና እንዲለማመዱ ማበረታታት፣

### 4.5.12 ኦቲስቲክ ለሆኑ ልጆች

- ጨዋታ፣
- ቋንቋ፣
- ማኅበራዊ ኑሮና □ደኝነት፣
- የሌላ ሰውን ሃሳብ ለመረዳት አይን ለአይን መተያየት፣
- አላስፈላጊ የሆኑ የአካል እንቅስቃሴዎችን መቆጣጠር፣
- ራስን የመርዳት ክሂሎች፣
- ሥነጥበብና ሙዚቃ፣
- ቅርፆችንና ቀለሞችን የመለየት ልምምዶችን እና የመሳሰሉትን ያካትታል።

### 4.5.13 ተደራራቢ የአካል ጉዳት ላለባቸው

እንደ ተደራራቢው የአካል ጉዳት አይነት ትምህርቱን በጨዋታ እያዋዙ ማስተማር፤ ለምሳሌ መስማት መሳንና አይነ ስውርነት በአንድ ላይ ከተከሰቱ የምናስተምረው ክህሎት የህጻናቱ መዳፍ፤ የተቀሩት የስሜት ህዋሳትና አስተሳሰቡ ላይ ማተኮር ይኖርበታል።

### 4.5.14 የስሜት መረበሽ ላለባቸው፣

- ማህበረሰባዊ ተቀባይነት ስላለው የቋንቋ አጠቃቀም፣
- መከባበር (ስለተዋለ ውለታ ማመስገን፤ አለመሳደብ፤አለመደባደብ ወዘተ)፣
- ንብረትን ከአደጋ መጠበቅ (የትምህርት ቤትን ንብረት ስለመንከባከብ፤ የሌሎች ተማሪዎችን ምሳ ዕቃ፤ መጫወቻና ቁሳቁስ አለመውሰድ ወዘተ)፣
- የጨዋታ ህጎችን ማክበርና ተራ ጠብቆ ስለመጫወት መጫወት፣
- □ደኅንነት ስለመመስረትና □ደኅንነትን ስለማቆየት እና የመሳሰሉትን ያካትታል።

### 4.5.15 ልዩ ተሰጥኦ ላላቸው

- ተሰጥኦዋቸውን ለማሻሻል እገዛ ማድረግ፣
- ሥነጥበብና ሙዚቃ፣
- ቋንቋ፣
- ቁሳቁሶችን እንደፍላጎታቸው በመስጠት እየተጫወቱ አዲስ ነገር እንዲፈጥሩ ማለማመድ፣
- ከልጆች ተለይተው በተለየ ቁስ ለብቻቸው መጫወት ሲፈልጉ መፍቀድ እና የመሳሰሉትን ያካትታል።

## 4.6 የቅድመ መደበኛ ትምህርት አመታዊ የትምህርት መርሀ ግብር /ካሌንደር/

የአንድ ዓመት የቅድመ መደበኛ ትምህርት መርሀ ግብር ከ203 – 206 ባሉት ቀናት ውስጥ የሚሰጥ ሲሆን መርሀ ግብሩ ለ30 ሳምንታት፤ በሣምንት ለ5 ቀናት ከሰኞ-ዓርብ ይካሄዳል። በአንድ ሣምንት የሚኖረው ክፍለ ጊዜያት 25 ሲሆን የአንድ ክፍለ ጊዜ ርዝማኔ 30 ደቂቃ ሆኖ በመካከል የ5 ደቂቃ የዝግጅት ጊዜ ይኖረዋል። የክፍለ ጊዜው ብዛት እንደ ሕፃናቱ ፍላጎት፣ ከአካባቢው ነባራዊ ሁኔታ እና ከትምህርቱ አቀራረብ ሁኔታ ጋር በማገናዘብ ሊሻሻል ይችላል።የቅድመ መደበኛ ትምህርት ፕሮግራም በሙሉ ቀን ይካሄዳል።በመጀመሪያ መንፈቀ አመት /ሰሚስተር/ መጨረሻ ላይ የቅድመ መደበኛ ትምህርት ተቋማት ለ15 ቀናት ዕረፍት ዝግ ይሆናሉ።

### 4.6.1 የቅድመ መደበኛ ትምህርት ፕሮግራም ደረጃዎች

በአፀደ ህፃናት የሚሰጠው የቅድመ መደበኛ ትምህርት መርሀ ግብር ለሶስት ተከታታይ አመት የሚሰጥ ሲሆን በሶስት ደረጃዎች የተከፈለ ነው።ደረጃዎቹም ከታች እንደሚከተለው ቀርበዋል።

DRAFT

ሀ.ለደረጃ አንድ 4 ዓመት ዕድሜ ላላቸው የአንድ ክፍለ - ጊዜ ርዝመት 25 ደቂቃ ሆኖ በክፍለ ጊዜያት መካከል የ5 ደቂቃ የዝግጅት ጊዜ ይኖረዋል።

ለ. ለደረጃ ሁለት 5 ዓመት ዕድሜ ላላቸው የአንድ ክፍለ - ጊዜ ርዝመት 25 ደቂቃ ሆኖ በክፍለ ጊዜያት መካከል የ5 ደቂቃ የዝግጅት ጊዜ ይኖረዋል።

ሐ. ለደረጃ ሶስት 6 ዓመት ዕድሜ ላላቸው/ የአንድ ክፍለ - ጊዜ ርዝመት 30 ደቂቃ ሆኖ በክፍለ ጊዜያት መካከል የ5 ደቂቃ የዝግጅት ጊዜ ይኖረዋል።

## 4.6.2 የክፍለ ጊዜያት ሥርጭት

ሰንጠረዥ 13 :- ሳምንታዊ የክፍለ ጊዜ ሥርጭት በደረጃ

| ተራ ቁ. | የፕሮግራም ዓይነት | አራት ዓመት* | አምስት ዓመት* | ስድስት ዓመት* | መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ጨዋታ | 10 | 10 | 8 | |
| 2 | ትምህርት | | | | |
| | ▪ ቋንቋ | 3 | 3 | 4 | |
| | ▪ የአካባቢ ትምህርት | 2 | 2 | 2 | |
| | ▪ ሂሣብ | 2 | 2 | 2 | |
| | ▪ ሙዚቃ | 2 | 2 | 2 | |
| | ▪ የሰውነት ማጐልመሻ | 2 | 2 | 2 | |
| | ▪ የሥነ ሥዕልና ቅርጻ ቅርጽ | 2 | 2 | 3 | |
| 3 | ሥራ (ግላዊና ማህበራዊ ጠቀሜታ ያለው) | 2 | 2 | 2 | |
| | **ድ ም ር** | **25** | **25** | **25** | |

*4 ዓመት ማለት ዕድሜያቸው 3 ዓመት ከስድስት ወር የሞላቸው/ያለፉቸውና እስከ 4 ዓመት ከ5 ወር የዕድሜ ክልል ውስጥ ያሉ ህጻናት ማለት ነው።

*5 ዓመት ማለት ዕድሜያቸው 4 ዓመት ከስድስት ወር የሞላቸው/ያለፉቸውና እስከ 5 ዓመት ከ5 ወር የዕድሜ ክልል ውስጥ ያሉ ህጻናት ማለት ነው።

*6 ዓመት ማለት 5 ዓመት ከስድስት ወር የሞላቸው/ያለፋቸውና እስከ 6 ዓመት ከ5 ወር የዕድሜ ክልል ውስጥ ያሉ ሕፃናት ማለት ነው።

በሃገራችን የልዩ ፍላጎት እና አካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን ዕድሜያቸው ለትምህርት እንደደረሰ ቶሎ ወደ ትምህርት ቤት የመላክ ልምድ በበቂ ሁኔታ የዳበረ አይደለም። በመሆኑም ተማሪዎቹንእንዳመጣጣቸው በመቀበል ከላይ ለተዘረዘሩት የፕሮግራም አይነቶች የተመደበውን የክፍለ-ጊዜ ስርጭት የህጻናቱን የጉዳት አይነት ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ተግባራዊ ማድረግ ይገባል።

**ማሳሰቢያ፣**

ሀ/ መደበኛውን የቅድመ መደበኛ ትምህርት ፕሮግራም መከታተል የሚችሉ ልዩ ፍላጐት ያላቸው ሕፃናት በተለየ ክፍል ውስጥ ሆነው ልዩ ክህሎቶችን ከተከታተሉ በኋላ ከሌሎች ጋር ተቀላቅለው በፕሮግራሙ ላይ ንቁ ተሳታፊ ይሆናሉ። ከሌሎች ጋር ተቀላቅለው ፕሮግራሙን እኩል መከታተል የማይችሉት ግን የተለየ ተጨማሪ ድጋፍና ክትትል እየተደረገላቸው አግባብነት ያለውን ፕሮግራም ይከታተላሉ።

ለ/ ለየቡድኑ የተሰጠው ክፍለ ጊዜ በዕለታዊ የፕሮግራም መርሃ ግብር ላይ እንደተመለከተው የጨዋታ፣ የትምህርትና የሥራ ጊዜ ርዝመት እንደ አስፈላጊነቱ የተለያየ መሆኑ ሊታወቅ ይገባል።በተለይም የአካል ጉዳት ያለባቸው ህጻናት ተጨማሪ ጊዜና ትኩረት እንደሚሹ መገንዘብ ያስፈልጋል።

ሰንጠረዥ 14 :- የዐጸደ ህጻናት ትምህርት ዕለታዊ መርሃ ግብር በደረጃ

| ተራ ቁጥር | የመርሀ ግብሩ ዓይነት | ደረጃ 1 | ደረጃ 2 | ደረጃ 3 |
|---|---|---|---|---|
| | | 4ዓመት | 5ዓመት | 6ዓመት |
| 1 | የመቀበያ ሰዓት | 2፡00 - 3፡00 | 2፡00 - 3፡00 | 2፡00 - 3፡00 |
| 2 | ለትምህርት ቅድመ ዝግጅት | 3፡00 - 3፡05 | 3፡00 - 3፡05 | 3፡00 - 3፡05 |
| 3 | ትምህርት | 3፡05 - 3፡30 | 3፡05 - 3፡30 | 3፡05 - 3፡35 |
| 4 | ለትምህርት ቅድመ ዝግጅት | 3፡30 - 3፡35 | 3፡30 - 3፡35 | 3፡35 - 3፡40 |
| 5 | ትምህርት | 3፡35 - 4፡00 | 3፡35 - 4፡00 | 3፡40 - 4፡10 |
| 6 | ለቁርስ ዝግጅትና ቁርስ | 4፡00 - 4፡40 | 4፡00 - 4፡40 | 4፡10 - 4፡50 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | መመገቢያ | | | |
| 7 | ዕረፍት/ነፃ ጨዋታ/ | 4፡40 - 5፡40 | 4፡40 - 5፡40 | 4፡50 - 5፡50 |
| 8 | የክፍል ውስጥ ጨዋታ | 5፡40 - 6፡05 | 5፡40 - 6፡05 | 5፡50 - 6፡20 |
| 9 | የክፍል ዝግጅት | 6፡05 - 6፡15 | 6፡05 - 6፡15 | 6፡20 - 6፡30 |
| 10 | የምሣ ዝግጅትና መመገቢያ | 6፡15 - 7፡15 | 6፡15 - 7፡15 | 6፡30 - 7፡30 |
| 11 | የመኝታ ሰአት | 7፡15 - 8፡15 | 7፡15 - 8፡15 | 7፡30 - 8፡30 |
| 12 | ከመኝታ መነሳትና መፀዳዳት | 8፡15 - 8፡30 | 8፡15 - 8፡30 | 8፡30 - 8፡45 |
| 13 | የትምህርት ቅድመ ዝግጅት | 8፡30 - 8፡35 | 8፡30 - 8፡35 | 8፡45 - 8፡50 |
| 14 | ትምህርት | 8፡35 - 9፡00 | 8፡35 - 9፡00 | 8፡50 - 9፡20 |
| 15 | የውጭ ጨዋታ | 9፡00 - 9፡50 | 9፡00 - 9፡50 | 9፡20 - 9፡50 |
| 16 | ወደ ቤት ሽኝት | 9.50-10.25 | 9.50-10.25 | 9፡50 -10፡25 |

**ማሳሰቢያ**

- በሣምንት ሁለት ቀናት ለትምህርት ከተያዘው ጊዜ ውስጥ የቡድን ሥራ የሚሠሩበት ሰዓት ይሆናል፡፡አካል ጉዳተኛ ተማሪዎችም ሊደግፏቸው ከሚችሉ □ደኞቻቸው ጋር እንዲሆኑ ቡድኑን የሚያደራጀው/የምታደራጀው መምህር/ት ማመቻቸት ያስፈልጋል፡፡
- የመርሐ ግብሩ መጀመሪያና የማጠናቀቂያ ሰዓት እንደየአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ተግባራዊ ሊሆን ይችላል፡፡

## 4.6.3 የመምህራን የሥራ ሰዓት

ሕፃናትን በአግባቡ ለማሳደግ፤ ለመንከባከብና ለመደበኛ ትምህርት በብቃት ለማዘጋጀት ለአንድ መምህር/ት በሳምንት የሚኖረው/ራት የሥራ ሰዓት መጠን የሕፃናቱ ምሳና መኝታ በየቤታቸው ከሆነ በሳምንት 30 ሰዓት ይሆናል፡፡በሳምንት ውስጥ ያለው 30 ሰዓት ድልድል እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

- 5 ሰዓት ጠዋት ሕፃናትን ለመቀበል፣
- 13 ሰዓት ከ20 ደቂቃ ለጨዋታ፤ ለትምህርትና ሥራ ነክ ለሆኑ ፕሮግራሞች፣

- 11 ሰዓት ከ40 ደቂቃ ለቁርስ፤ለእረፍት፤ ለክፍል ዝግጅትና ለመሸኛ የሚውለውን ጊዜ ያጠቃልላል።

ለሕፃናት ምግብና መኝታ በአፀደ ሕፃናቱ ውስጥ የሚሰጥ ከሆነ በሳምንት 40 ሰዓት ይሆናል።

ይህም በዝርዝር ሲታይ፣

- 5 ሰዓት ጠዋት ሕፃናትን ለመቀበል፣
- 13 ሰዓት ከ20 ደቂቃ ለጨዋታ፤ ለትምህርትና ሥራ ነክ ለሆኑ ፕሮግራሞች፣
- 21 ሰዓት ከ40 ደቂቃ ለቁርስ፣ለምሳ፣ለመፀዳዳት፣ ለመኝታ፣ ለእረፍት፣ ለክፍል ዝግጅትና ለመሸኛ የሚውለውን ጊዜ ያጠቃልላል።

## 4.7 የትምህርት ቋንቋ፣የማስተማርና የምዘና ዘዴዎች

### 4.7.1 የትምህርት ቋንቋ

የቅድመ መደበኛ ትምህርት የማስተማሪያ ቋንቋ የአፍ መፍቻ ቋንቋ መሆን ይኖርበታል።

### 4.7.2 የማስተማሪያ ዘዴዎች

በቅድመ መደበኛ ፕሮግራም ለሕፃናት በጨዋታ መልክ የሚሰጣቸው ተግባራት ከሕፃናቱ የአእምሮና የአካል ብቃት/ ልዩ ፍላጎት ወዘተ. ጋር የሚጣጣሙና ለወደፊት ዕድገታቸው የጐላ አስተዋፅኦ የሚያደርጉ መሆን አለባቸው። በዚህ ደረጃ ለሕፃናት የሚሰጠው መደበኛ ትምህርት ሳይሆን ለሕፃናቱ ዕድገት መሠረት የሚሆኑ ተግበራት ስለሆኑ የሚካሄዱ እንቅስቃሴዎች በሙሉ የሕፃናትንና የመምህራንን የጋራ ተሳትፎ የሚጠይቁ ናቸው። ስለሆነም በግልም ሆነ በጋራ እንዲካሄዱ የሚዘጋጁ እንቅስቃሴዎች የሕፃናትን የአካል፣የአእምሮ፣የስሜትና ማህበራዊ ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ የሚያስገቡ መሆን አለባቸው።

ጥናቶች እንደሚያመለክቱት ህፃናት የበለጠ ውጤታማ የሚሆኑት ለእነርሱ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች በተለያዩ የማስተማር ዘዴዎች ተደግፈው ሲቀርቡ ነው።

በዚህ ደረጃ መምህራን የሚከተሉትን የማስተማር ዘዴዎችን ሊጠቀሙ ይችላሉ።

- የቡድን ጫወታ
- የግል ጫወታ
- ሚና ጫወታ
- መስሎ ጨዋታ
- ሠርቶ ማሳየት
- የመስክ ጉብኝት /በመምህራን የቅርብ ክትትል/ ማወያየት፣

- የቃል ዘገባ / የምልክት ቋንቋ ዘገባ
- ገለጻ /ሕፃናትን አሳታፊ የሆነ ወዘተ. ናቸው።

በጨዋታ፣ በስራ እና በትምህርት ወይም በማናቸውም ሁኔታ ህፃናት ከአካላዊ፣ አእምሯዊ፣ ስሜታዊ፣ ወዘተ. ጉዳቶች/ ጥቃቶች መጠበቅ ይኖርባቸዋል።

### 4.7.3 የምዘና ዘዴዎች

ጥናቶች እንደሚያመላክቱት እያንዳንዱ/ዱ ህፃን የተለየች በመሆኗ/ኑ የምዘና ዘዴዎች ይህንን ከግምት ውስጥ በማስገባት በውድድር ላይ የተመሰረተ ሳይሆን የእያንዳንዱን/ዱን ህፃን የመማር ፍላጎት ልዩነትና አቅምን ግምት ውስጥ በማስገባት ከራሷ/ራሱ ጋር ብቻ የምትወዳደርበትን /የሚወዳደርበትን ስልት ቀይሶ ተግባራዊ ማድረግ ይገባል።በመሆኑም ህፃናት ደረጃው የሚጠይቀውን ተፈላጊ ብቃት እንዲያሟሉ በተከታታይ ምዘናዎች እና የእያንዳንዱን/ዱን ህፃን የዕለት ውሎ በማህደረ ተግባር መዝግቦ በመያዝ ውጤታቸውን ሂደታዊ በሆነ መንገድ ማጠናቀር ይገባል። ይህም ማለት በቅድመ መደበኛ ትምህርት ፕሮግራም ሕፃናት የሚመዘኑት/የሚገመገሙት ፈተና በመስጠት ሣይሆን በተከታታይ የምዘና ዘዴ ነው።

የውጤት አሰጣጥን በተመለከተ በቁጥር፣ በመቶኛ  ወይም በመሳሰለው መንገድ ሳይሆን አጠናቋል/አጠናቃለች ተብሎ መሰጠት ይኖርበታል።

### 4.7.4 ክፍል መድገምን በተመለከተ

- ማንኛውም ህፃን ክፍል መድገም አይኖርበትም/ባትም ። ሆኖም ግን በትምህርት አቀባበሉ/ሏ ፈጣን ላለሆኑ ህጻናት ሲያጋጥሙ ተጨማሪ ድጋፍ እና ክትትል ማድረግ ይገባል።

### 4.7.5 ከክፍል ክፍል ዝውውር

- አንድ/ዷ ትህጻን የአንድ ዓመት መርሀግብር ካጠናቀቀ/ች በኋላ ወደ ቀጣዩ ደረጃ ያልፋል/ ታልፋለች።

### 4.7.6 የተማሪ ቅበላን በተመለከተ

- ማንኛውም የቅድመ መደበኛ ትምህርት ተቋም ያለውን የቅበላ አቅም  መሰረት አድርጎ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ልዩነት ሳያደርግ ሁሉንም ህጻናት (የልዩ ፍላጎት ህፃናትን ጨምሮ) ተቀብሎ የማስተማር ግዴታ አለበት።

DRAFT

### 4.7.7 የማበረታቻ እና የምስክር ወረቀት

- ለህጻናት የሚደረጉ ማናቸውም አይነት ማበረታቻዎች የህፃናቱን ስሜት የማይጎዱ መሆን ይኖርባቸዋል።
- ህፃናት በየደረጃው ያለውን መርሀ ግብር ሲያጠናቅቁ የምስክር ወረቀት ሊሰጣቸው ይገባል።

### 4.7.8 ግላዊ መረጃ አያያዝን በተመለከተ

ትምህርት ቤቱ የህፃናትን ግላዊ ነፃነት ማከበር ይኖርበታል ። በመሆኑም ህፃናትን የተመለከቱ እና ሌሎች ማወቅ የማይገባቸውን መረጃዎች ሚስጥራዊነት መምህራን እና ጉዳዩ በቀጥታ የሚመለከታቸው አካላት  የመጠበቅ ሀላፊነት አለባቸው።

DRAFT

# ክፍል አምስት

## 5.ከቅድመ መደበኛ ትምህርት መምህራን እና ህፃናት የሚጠበቅ ባህርይ እና የመምህራን የትምህርት ዝግጅት፣

### 5.1 ከቅድመ መደበኛ ትምህርት መምህራን የሚጠበቅ ባህርይ

- ርህራሄ
- ትዕግስት
- ለህፃናት ልዩ ፍቅር ያላቸው
- ደባል / ሱስ የሌለባቸው
- ጥሩ ስነምግባር ያላቸው
- ለሙያው ፍቅርያላቸው
- ልዩ ፍላጎት ያላቸውን (ተሰጥኦ ያላቸውን ጨምሮ) ህጻናት ለመረዳትና ለመደገፍ ፍላጎት ያላቸው፣
- የአካባቢውን ባህልና ወግ የሚያውቁ እና የሚያከብሩ መሆን ይኖርባቸዋል።

### 5.2 የቅድመ መደበኛ መርሐ-ግብርን ያጠናቀቁ ሕፃናት ባህርይ፣

- ሆሄያትንና አሃዞችን በሥርዓት መለየትና መቅረጽ፣ ተራን ጠብቆ ሃሣብን መግለጽና ማዳመጥ ይችላሉ፣
- በአካልና በአእምሮ የበለፀጉ፣ ስሜትን መግለጽና ውበት ማድነቅ ይችላሉ፣
- ለምርምር፣ለፈጠራና ለሥራ ፍቅር ያላቸው፣ በራሳቸው የሚተማመኑና በሥነ ሥርዓት የታነፁ ይሆናሉ፣
- በአካባቢያቸው በደረጃቸው በማህበራዊ ኑሮ ለመሳተፍ የነቁና የተዘጋጁ ይሆናሉ፣
- ለመደበኛ ትምህርት ቤት እና ለወደፊት ህይወታቸው የተዘጋጁ ይሆናሉ፣

ስለራሳቸው ያላቸው ግንዛቤ እና ከሌሎች ጋር የርስ በርስ ግንኙነት የማድረግ ክሂላቸው የዳበረ ይሆናል።

### 5.3 የትምህርት ዝግጅት

የቅድመ መደበኛ ትምህርት መምህራን የአፍ መፍቻና የእንግሊዝኛ ቋንቋዎችን ጨምሮ ስለሚያስተምሩት ትምህርት ይዘት፣ ስለሚያስተምሩዋቸው ሕፃናትና በመካከላቸው ሊኖሩ ስለሚችሉ የችሎታና የፍላጐት ልዩነቶች እንደዚሁም ለልዩነቶቹ አያያዝ አስፈላጊ የሆኑ

ሙያዊ እውቀትና ክህሎት ሊኖራቸው ይገባል። ከዚህ በተጨማሪ በሙያዊ ተግባር ክንውን ሂደት ይህን እውቀታቸውንና ክህሎታቸውን ከተገቢው ሙያዊ ሥነ ምግባር ጋር በማቀናጀት በሕፃናት እንቅስቃሴ ፕሮግራም ላይ በተሟላ መልክ መሳተፍ ይገባቻዋል።

ለቅድመ መደበኛ ፕሮግራሙ የሚሆኑ ክንውኖችን ከሕፃናት የአካል ፣የስሜትና ማህበራዊ ወዘተ. ዕድገት ጋር በማገናዘብ ሥራ ላይ ሊውሉ የሚችሉትን በማቀድ ተግባራዊ ማድረግ አለባቸው።የቅድመ መደበኛ ትምህርት መምህራንበቅድመ መደበኛ ትምህርት መምህርነት ዲፕሎማ ሊኖራቸው ይገባል።

DRAFT

# ክፍል ስድስት

## 6. ከአፀደ ህጻናት ትምህርት ጋር የተያያዙ ልዩ ልዩ ጉዳዮች

### 6.1 የአጠቃላይ ትምህርት ኢንስፔክሽን አገልግሎትን ስለማግኘት

*የቅድመ መደበኛ ትምህርት ተቋም / አፀደ ህፃናት በአጠቃላይ ትምህርት ኢንስፔክሽን መመሪያ እና ማዕቀፍ ላይ የተቀመጡ አሰራሮችን ተግባራዊ ማድረግ ይኖርበታል።*

*በመሆኑም :-*

- *ተቋሙ በሶስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ቢያንስ አንድ ጊዜ በኢንስፔክሽን ሂደት በማለፍ ደረጃውን ማሻሻል ይጠበቅበታል።*
- *ተቋሙ በኢንስፔክሽንምዘና ደረጃ 1 ወይም ደረጃ 2 ላይ ከሆነ ከአንድ አመት በኋላ በድጋሚ ኢንስፔክሸን መታየት ይኖርበታል።*
- *ተቋሙበኢንስፔክሽንምዘና ደረጃ 3 ወይም ደረጃ 4 ካገኘ በኋላ ቢያንስ በየሶስት አመቱ አንድ ጊዜ በኢንስፔክሽን መታየት ይኖርበታል።*

### 6.2 የሰንደቅ አላማ አከባበር

- *የኢትዮጵያ እና የክልል ሰንደቅ ዓላማዎች መስቀያ ቦታ በትምህርት ቤቱ አማካይ ቦታ መኖር አለበት።*
- *ህፃናት ተማሪዎች የአገር ፍቅር እንዲኖራቸው በትምህርት መጀመሪያ እና ማጠናቀቂያ ላይ የኢትዮጵያና የክልሉን ብሔራዊ መዝሙር ተሰልፈው በመዘመር የባንዲራ መስቀል እና ማውረድ ስነስርዐት መከበር ይኖርበታል።*
- *የኢትዮጵያ ባንዲራ መስቀያ ሰንደቅከክልሉ ባንዲራ መስቀያ ሰንደቅ በመጠኑ መብለጥ ይኖርበታል።*

## 6.3 በቅድመ መደበኛ ትምህርት ተቋም መገኘት ያለባቸው የስርአተ ትምህርት መሳሪያዎች፣ መመሪያዎች፣የትምህርት እና ህግ ነክ ሰነዶች

### 6.3.1 መመሪያዎች

- *የትምህርት እና ስልጠና ፖሊሲ፣*
- *የአጠቃላይ ትምህርት ሥርዓተ ትምህርት ማዕቀፍ፣*
- *የአፀደ ህፃናት መርሀ ትምህርት ማዕቀፍ ፣*
- *የአ ክፍል የመምህር/ት መምሪያ፣*

- በአካባቢ ሳይንስ፣በቋንቋ እና በሂሳብ ለሶስቱ ደረጃዎች መጻህፍት፣
- የተማሪው የንባብ፤ የተረትና ሥዕላዊ መጻሕፍት፣
- ልዩ ልዩ የት/መርጃ መሣሪያዎች፣
- የቅድመ መደበኛ ትምህርት መመሪያ፣
- የልዩ ፍላጎት - አካቶ ትምህርት የአፈጻጸም መመሪያ
- የአካቶ ትምህርት የድጋፍ መስጫ ማዕከላትን ለማቋቋም እና ለመምራት የተዘጋጀ መመሪያ፤

## 6.3.2 ሕግ ነክ ሰነዶች

- ዓለም አቀፍ የሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽን፣
- የትምህርት ሕግ፣
- የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ፣
- ስለግል የት/ተቋሞች ፈቃድ አሰጣጥና ቁጥጥር የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ፤
- የማዕከልና/የክልል አሰፈጻሚ አካላትን ሥልጠን ለመወስን የወጣ አዋጅ 4/71/98
- የተሻሻለው አዲሱ የሠራተኞች ህግ አዋጅ ቁጥር 377/1996
- የልዩ ፍላጎት ትምህርት ስትራቴጂ ።

DRAFT

# ክፍል ሰባት

## 7. የትምህርት አመራር፣ የወላጆች እና የህብረተሰቡ ሚና

### 7.1 የአመራር ሚና

የትምህርት አመራርና አስተዳደር ባልተማከለ መንገድ የሚካሄድና የአካባቢውን ማኅበረሰብ ንቁ ተሳትፎ የሚጠይቅ ነው።የቅድመ መደበኛ ትምህርት ተቋማት አመራርና አስተዳደር የተቋማቱን፣ የወላጆችንና የአካባቢውን ማኅበረሰብ አባላት እና ባለድርሻዎች ያቀፈና ዲሞክራሲያዊ ተሳትፎን ተግባራዊ የሚያደርግ ሲሆን ተሳትፏቸውን በሚከተሉት መድረኮች ሊገልጹ ይችላሉ።

- በቅድመ መደበኛ ትምህርት ተቋም ኮሚቴ ወይም ቦርድ ውስጥ ኅብረተሰቡን በመወከል፣
- በቅድመ መደበኛ ትምህርት ተቋም የወላጅ ኮሚቴ ውስጥ ወላጆችን በመወከል፣

### 7.2 የወላጆች ሚና

የወላጆች ተሳትፎ በትምህርት ቤት ውስጥ ለልጆች ስኬታማነት አስተዋጽዖ ከሚያበረክቱት በጣም ጉልህ ነገሮች መካከል አንዱ እንደሆነ ጥናቶች ያመለክታሉ። ወላጆች በልጆቻቸው ትምህርት ላይ መሉ ተሳትፎ በሚያደርጉበት ጊዜ የተማሪዎች የውጤት ደረጃ ያድጋል የልጆቻቸው ከትምህርት ገበታ ላይ የመቅረት ሁኔታ ይሻሻላል። እንደዚሁም የቤት ሥራዎቻቸውን በወቅቱ እንዲሠሩ ከመርዳቱ ሌላ ለባህርያቸው መሻሻልም ትርጉም ያለው አስተዋፃኦ ይኖረዋል።

ስለትምህርት ያላቸው ዝንባሌም የበለጠ አዎንታዊ ይሆናል። ይህም በበኩሉ ተማሪዎች ሳያቋርጡ ትምህርታቸውን በማጠናቀቅ ለከፍተኛ ውጤት እንዲበቁ ያስችላል።

በቅድመ መደበኛ ትምህርት ተቋማት የሚገኙ ህፃናት በአካል፣ በአእምሮ፣በማኅበራዊና በስሜት ገና ያልዳበሩ በመሆናቸው ኃላፊነቱን ሙሉ ለሙሉ ለተቋማቱ ከመተው ይልቅ ወላጆች በተቋማቱ በመገኘት የቅርብ ክትትልና ድጋፍ ሊያደርጉ ይገባል።

ሕፃናት በቅድመ መደበኛ ትምህርት ተቋማት መሳተፍ ለወደፊት ሕይታቸው መሠረት የሚጣልበት ሲሆን፣ ፕሮግራሙን ለማካሄድ የሚያስፈልገውን ወጪ መንግሥት ብቻውን ስለማይችል ወላጆች እነዚህን ተቋማት በገንዘብና በማቴሪያል በመደገፍ የሕፃናቱ የተሟላ አገልግሎት እንዲያገኙ ወላጆች የበኩላቸውን ድርሻ መወጣት ይጠበቅባቸዋል።

DRAFT

## 7.3 የህብረተሰብ ሚና

*የቅድመ መደበኛ ትምህርት ተቋማትን ከማጠናከር ፣ ከመደገፍ እና በባለቤትነት መንፈስ ከመምራት አኳያ በህብረተሰቡ እና በተቋሙ መሀከል የተጠናከረ ግንኙነት ሊኖር ይገባል።*

*የዚህም ዋና ዋና ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው።*

- *የቅድመ መደበኛ ትምህርት ተቋም ምን እየሠራ እንዳለና የፕሮግራሙን ዓላማዎች ተግባራዊ ለማድረግ ሃሣብ ለማካፈል፣ ለምሳሌ የቅድመ መደበኛ ትምህርት ተቋሙ ኃላፊነቱን በብቃት እየተወጣ መሆኑንና ስለ ዓላማውና የዓላማውን ተግባራዊነት ለኅብረተሰቡ ማሳወቅ ከኅብረተሰቡ የሚሰጡ አስተያየቶችን መሠረት በማድረግ የተቋሙን የሥራ አመራር ሥራውን እንዲያሻሽል ለማድረግ፣*
- *ሕፃናቱ በፕሮግራሙ ስላላቸው ተሳትፎና ውጤት ወላጆች አውቀው ተገቢውን ክትትል ለማድረግ፣*
- *የወላጆችንና የመምህራንን ግንኙነት ለማጠናከርና የፕሮግራሙ ውጤት ይበልጥ የተሻለ እንዲሆን ለማስቻል*
- *በቅድመ መደበኛ ትምህርት ተቋም ኮሚቴ ወይም ቦርድ ውስጥ በመሳተፍ፣*
- *ተቋሙን ለማጠናከር በሚቀርብ ዕቅድ ላይ ውይይት በማካሄድ መርምሮና አሻሽሎ ለማጽደቅ እና አፈጻጸሙንም ለመከታተልና ለመቆጣጠር*
- *ሥርዓተ ትምህርቱ ከአካባቢው ሁኔታ ጋር ተጣጥሞና ተዛምዶ ለሕፃናቱ መቅረቡን ለመከታተልና ሃሣብ ለመስጠት... ወዘተ ይሆናል።*

DRAFT